# ቅንጅት ስሙን መለወጡን አስታወቀ

በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም የተዋሐደው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ስሙን በመለወጥ **የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት** ተብሎ ለመጠራት መወሰኑን ነሐሴ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በይፋ አስታወቀ።

ይህንኑ ቅንጅት ስሙን መለወጡን ያስታወቀበትን ስብሰባ የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጋራ የመራ ሲሆን በዕለቱ አቶ አባይነህ ብርሃኑ የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የፕሬዘዳንቱ ተወካይ፤ ወ/ሮ ዓለማየሁ ሞገድ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፤ አቶ አባተ ተገኝ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የማህበራ ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ እንዲሁም ወጣት ጌታቸው አበበ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን ለማዳን የተከፈለውን መስዋዕትነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያጣውን የሕግ የበላይነት ለማምጣት ፓርቲው የሚጠብቀውን ከፍተኛ ትግል በማስመልከት በየተራ ሰፊ ገለጻ አድርገዋል።

በዕለቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በመወከል በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ በሚገኘው በፓርቲው ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለተሰበሰቡት ለፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ይህንኑ የቅንጅት ስም መለወጡን ያስታወቁት ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣው የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ አባልና የሕዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ ናቸው።

ወ/ሪት መሶበወርቅ በዚህ ወቅት ባሰሙት ንግግር ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከጥምረቱ አንስቶ እስከ ዛሬ ለሕዝብ ነጻነት፤ ለሰላም፤ ለፍትህ እንዲሁም ለዴሞክራሲ በተከታታይ የከፈለውን መስዋትዕነት በዝርዝር አስታውሰው አያይዘውም ቅንጅት የሚለው ስያሜ ከሌላ አዲስ ከተፈጠረ ድርጅት መስጠቱን በማስመልከት ሲናገሩ "…በምርጫ 97 ቅስቀሳ ያካሔድንበትን፤ የተወዳደርንበትን፤ ለአምስት ዓመታት የተመረጥንበትን፤ የታሰርንበትን፤ የከሰስንበትን፤ ሌሎችንም መሥዋዕትነቶችን ሁሉ የከፈልንበትን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተሰኘውን ስማችንን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለሌላ አካል ስለሰጠብን አምርረን ተቃውመናል "ብለዋል።

ሰኔ 14ና 15 ቀን 2000 ዓ.ም የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድን ያስታወሱት ወ/ት መሶበወርቅ በማያያዝ ደግሞ ያሁኑን የፓርቲውን ስም ለመምረጥ የተደረጉትን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሲያብራሩ "እኛም ጠቅላላ ጉባዔው የሰጠንን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የሥም ለውጥ ለማድረግ መንቀሳቀስ ጀመርን። በዚህም መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ አባላትና ደጋፊዎች በቀጥታ ስም በማውጣቱ ሒደት እንዲሳተፉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጥሪ አቀረበ። በመሆኑም ከ70



EthioLion.Com

በላይ ስሞች ከተለያዩ ስፍራዎች ወደ ዋናው የፓርቲው ጽ/ቤት ተላኩ። ከተላኩት አማራጭ ስሞች መካከል "የመላው ኢትጵያ አንድነት ድርጅት" የሚለው የፓርቲ ስያሜ በአባላትና በደጋፊዎች በከፍተኛ ድምጽ ድጋፍ ያገኘ መሆኑን ወደ ፓርቲው ከመጡት የስያሜው ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል። በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴም እንደዚሁ በሙሉ ድምጽ ሊመረጥ ችሏል" በማለት አስረድተዋል።

አቶ የወንድ ወሰን ተሾመ በበኩላቸው አዲሱን የፓርቲውን ስያሜ ለመምረጥ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጊዜያዊ የአስመራጭ ስሞች አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋምና የመምረጫ መመዘኛዎችን በማዘጋጀት ሥራውን በከፍተኛ ጥንቃቄና በኃላፊነት ስሜት ማከናወኑን በማስረዳት ገለጻ አድርገዋል።

እንደዚሁም አቶ ዐባይ ብርሃኑ ከስብሰባው ተሳታፊዎች ለተነሱት በርካታ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጥተዋል።

በዕለቱ ወደ 350 የሚጠጉ አባላትና ደጋፊዎች በስብሰባው ላይ የተሳተፉ ሲሆን ጠንካራ የድጋፍ አስተያቶች ከተሰጡ በኋላ ሁሉም ባንድ ድምጽ **የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት** የሚለውን ስያሜ መቀበላቸውን አረጋግጠዋል።

EthioLion.com